## የአፈጻጸም ስልቱ እንዴት ነው?

ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን የሰሊጥ ምርት እና ግብይት ክላስተሮችን መሰረት ያደረገ ድጋፍ ያደርጋል:: በአሁኑ ጊዜ የሰሊጥ መረብ 38 ክላስተሮችን ያቀፈ ሲሆን ከእነዚህ ክላስተሮች መካከል 20ዎቹ በትግራይ ክልል 18ቱ ደግሞ በአማራ ክልል ይገኛሉ:: በሁለቱም ክልሎች ስር የሚገኙ ክላስተሮች በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በተዋቀረው የግብርና ክላስተር ውስጥ ይገኛሉ:: ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን የሚደግፈው የግብርና ሰብል ሰሊጥ እና የሰሊጥ ፈረቃ ሰብሎችን ሲሆን የስራ ቦታው ደግሞ ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ነው:: ፕሮጀክቱ በሰሊጥ እሴት ሰንሰለት ምርታማነትና የምርት ጥራት በመጨመር እንዲሁም የሰሊጥን ገበያ በማልማት የአርሶ አደሩን ገቢ ለመጨመር የሚያስችሉ አማራጮችን በመለየት ድጋፍ ያደርጋል::

## የድጋፍ አገልግሎቶቹ ምንድን ናቸው?

ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረቡን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ የድጋፍ አገልግሎቶች ይሰጣል:: እነርሱም 1ኛ) አዳዲስ አሰራሮችን ማፍለቅ 2ኛ) የባለድርሻ አካላትን አቅም መገንባት 3ኛ) ቴክኖሎጂዎችን እና አዳዲስ አሰራሮችን ማስፋፋት እና 4ኛ) አዳዲስ አሰራሮች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ተቋማዊ ማድረግ ናቸው::

## የፕሮጀክቱ ሰራተኞች እና አስተዳደር

በአማራ እና ትግራይ ክልል ግብርና ምርምር ተቋማት ስር የሚገኙ የጎንደር እና ሁመራ ግብርና ምርምር ማዕከላት የቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን ድጋፍ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቶች የሚገኙባቸው ማዕከላት ናቸው: የፕሮጀክቱ ሰራተኞች የእጽዋት ሳይንስ፣ የግብርና ምጣኔ ሀብት እና የኮሙዩኒኬሽንስና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ናቸው:: ከነዚህ በተጨማሪ በኒዘርላንድስ ከቫገኒንገን ዩንቨርሲቲ ሴንተር ፎር ዴቨሎፕመንት ኢኖቬሽንስ (ሲ ዲ አይ) ከፍተኛ ባለሙያዎች በማማከር እና በአስተዳደራዊ መስኮች ድጋፍ ያደርጋሉ::

የድጋፍ ፕሮጀክቱ ከጥር 2008 ዓ.ም ጀምሮ ከሌሎች ሦስት ፕሮጀክቶች ጋር በመጣመር ቤኔፊት በመባል በሚጠራው ፕሮግራም ስር እየሰራ ይገኛል:: ሌሎቹ ሶስት ፕሮጀክቶች ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር፣ በመገምገም እና በማስፋፋት ላይ የሚሰራው (ካስኬፕ)፣ በተቀናጀ የምርጥ ዘር አቅርቦት ላይ የሚሰራው (አይ ኤስ ኤስ ዲ) እና በግብርና ንግድ ልማት ላይ የሚሰራው (ኢንታግ) ናቸው::

## ምስጋና ከቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን!

የቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን ፕሮጀክት ሰራተኞች የኔዘርላንድስ መንግስት አዲስ አበባ በሚገኘው የሀገሪቱ ኤምባሲ በኩል ላደረገው የገንዘብ ድጋፍ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ:: ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ካሉ መንግስታዊ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበትና በጋራ እየሰራ ይገኛል:: የአማራ እና ትግራይ ክልል ግብርና ምርምር ተቋማት በዚህ ረገድ ከፍተኛ ምስጋና ይገባቸዋል:: ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን ከኤስ ኤን ቪ ፕሮጀክቶች ሲ ፎር ሲ እና አግሪቴራ ከቱስኬል ፕሮጀክት እና ኮመንሴንስ ከተባሉ አጋር ድርጅቶች ጋር ውጤታማ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል::




አድራሻ:- ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን
ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል
ፖ.ሣ. ቁ: 1337, ቀበሌ 16,
ጎንደር፣ ኢትዮጵያ

ስልክ: + 251 911 11 3897
+ 251 912 86 1076
+ 251 918 70 9240

http://sbnethiopia.org/
sbnethiopia@gmail.com




# SBN

# የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ

## ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ


http://sbnethiopia.org/
sbnethiopia@gmail.com

## ሰሊጥ ለምን ተመረጠ?

ሰሊጥ በሃገራችን በግብርናው ዘርፍ እድገት ለማምጣት በመንግስት ከተመረጡ ስድስት የሰብል ዓይነቶች መካከል አንዱ ነው:: ኢትዮጵያ በሰሊጥ ምርቷ በአለም አራተኛ ስትሆን ሰሊጥን ወደ ውጭ ከሚልኩ አገሮች መካከል ደግሞ የሁለተኛ ደረጃን ይዛ ትገኛለች:: በ2006 ዓ.ም ወደ ውጭ ከተላከ የሰሊጥ ምርት ወደ 600 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ተችሏል:: ሀገሪቱ በሰሊጥ ዘርፍ የተሻለ ገቢ እያገኘች ቢሆንም ከዚህ በተሻሻለ መንገድ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል ዓቅምና አማራጮች አሏት::

## የሰሊጥ መረብ (ኤስ ቢ ኤን) ምን ማለት ነው?

የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ በተለምዶ ኤስ ቢ ኤን በሚል የእንግሊዝኛ ምሕፃረ ቃል የሚጠራው በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሚገኙ አገር በቀል ስራ ፈጣሪዎችና ባለድርሻ አካላት የሚመራ ባብዛኛው ኢመደበኛ የሆነ የሰሊጥ ምርትና ግብይት ትስስር ነው:: የመረቡ ባለድርሻ አካላት ዓላማ ተወዳዳሪ፣ ቀጣይነት ያለዉና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት አሳታፊ የሆነ የሰሊጥ እሴት ሰንሰለት እንዲኖር መስራት ነው::

## የመረቡ ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው?

- **ዋናዎቹ የመረቡ አንቀሳቃሾች:-** አርሶ አደሮች፣ የሰሊጥ ነጋዴዎች፣ የሰሊጥ ምርት አቀናባሪዎች፣ ማህበራትና ዩንየኖች፣ አስመጪና ላኪዎች ...
- **ደጋፊዎች:-** አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትና ባንኮች፣ የቀን ሰራተኞች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች...
- **ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩና የሚያመቻቹ:-** አስተዳደር፣ ግብርና፣ ግብርና ምርምር፣ የንግድ፣ የትራንስፖርት፣ የማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽህፈት ቤቶች፣...



## የሰሊጥ መረቡ መሰረቶች እነማን ናቸው?

- 12 ወረዳዎች 4 ዞኖች 2 ክልሎች
- ከ70 በላይ የአርሶ አደሮች ህብረት ስራ ማህበራት
- 6 የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች
- ከ68,000 በላይ አርሶ አደሮች
- ከ2,000 በላይ ባለሃብት አርሶ አደሮች
- 540,000 የቀን ሰራተኞች
- 500,000 ሄክታር የሰሊጥ ማሳ
- 2 የግብርና ምርምር ማዕከላት
- ከ30 በላይ የወረዳ ግብርና፣ ማህበራት ማስፋፊያ፣ ንግድና ትራንስፖርት ጽህፈት ቤቶች
- የመንግስት እና የግል ባንኮች እና አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት

## ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን

ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን ማለት የሰሊጥ መረብ ባለድርሻ አካላት ያለሙት ግብ እንዲሳካ የሚያደርጉትን ጥረት የሚደግፍ ፕሮጀክት ነው:: ከዚህ ቀደም በነበረው የፕሮጀክቱ ምዕራፍ የሰሊጥ ምርት እና ግብይት መረብ የድጋፍ ፕሮግራም በመባል ይታወቅ የነበረ ሲሆን በአዲሱ ምዕራፍ ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን ፕሮጀክት በመባል ይጠራል::

## የቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን ግብ እና ዓላማዎች

የሰሊጥ መረብና የድጋፍ ፕሮጀክቱ ግብ ተወዳዳሪ፣ ቀጣይነት ያለውና ሁሉን አሳታፊ የሆነ የሰሊጥ ዘርፍ ልማት በማካሄድ የአርሶ አደሮችን ገቢ መጨመር ነው:: እዚህ ግብ ላይ ለመድረስ ሦስት ተቀዳሚ አላማዎችና ዘጠኝ ንኡስ ውጤቶች ተቀምጠዋል:: እነርሱም:-

1) የምርት ወጭን መቀነስ
   - ምርት እና የምርት ጥራትን ማሳደግ
   - በአጨዳ፣ በማጓጓዝ እና በመጋዝን አካባቢ የሚከሰቱ የምርት ብክነቶችን መቀነስ
   - ለአርሶ አደሮች የተሻለ የግብዓት ብድር ማቅረብ

2) የምርት እና ገበያ ልማት
   - የድህረ ምርት እሴትን መጨመር
   - የተሻሻለ የገበያ ትስስር እና ሽያጭ እንዲኖር መስራት
   - ለሰሊጥ ንግድ የብድር አቅርቦትን ማሻሻል

3) ለሰሊጥ ዘርፉ መጠንከርና እድገት የተመች ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ
   - በምርጥ ተሞክሮ ላይ የተመረኮዘ መረጃ ማቅረብ
   - የባለድርሻ አካላትን አቅም ማሳደግ
   - የባለድርሻ አካላትን ቅንጅት ማጠናከር

## የሰሊጥ መረብ የት ነው የሚገኘው?

የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በአማራና ትግራይ ክልሎች የሚገኙ አስራ ሁለት ወረዳዎችን ያካለለ ነው:: በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር እና አዊ ዞኖች በሚገኙ በቋራ፣ መተማ፣ ታች አርማጭሆ፣ ጠገዴ፣ ምዕራብ አርማጭሆ እና ጃዊ ወረዳዎች የተካተቱ ሲሆን፡ በትግራይ ክልል ደግሞ በምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖች በሁመራ፣ ጸገዴ፣ ወልቃይት፣ በታህታይ አዲያቦ፣ ጸለምቲ እና አስገደ ጽምብላ ወረዳዎችን ያካትታል::

